# የዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ አፈፃፀም መመሪያ

## ቁጥር 844/2014

# የዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ

## መመሪያ ቁጥር 844/2014

የዱር እንስሳት ሃብት ባልተቀናጀና አግባብነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና ለአደጋ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ፤

በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት ላይ የሚደረገው የንግድ የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እነዲከናወን ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዱር እንስሳት በፍጆታዊ እና ኢ-ፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል የወጡትን የዱር እንስሳት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17 (2) በተደነገገው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 844/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/199 ነው፤
2. **"ደንብ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፤
3. በአዋጁ እና ደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
4. **"ፈቃድ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የዱር እንስሳትን ለማጥመድና ለመነገድ ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
5. **"የዱር ሕይወት የመኖሪያ አካባቢ"** ማለት የየብስ፣ የውሃ አካል ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር ሕይወት የሚኖሩበት የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጪ ያለ ሥፍራ ነው፤
6. **"የዱር እንስሳት በህይወት ንግድ"** ማለት የዱር እንስሳት ወደ ውጭ መላክ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት መልሶ ወደ ውጭ መላክ ወይም እነዚህኑ የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት የንግድ ልውውጥ ነው፤
7. **"ማጥመድ"** ማለት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የዱር እንስሳትን ከነህይወታቸው መያዝ ነው፤
8. **"ማሯሯጥ"** ማለት እንስሳውን ለተወሰነ ደቂቃ ብቻ አሳዶ ገመድ አንገቱ ውስጥ በማስገባት አደገኛነቱን ቀንሶ እንዲያዝ ማድረግ ማለት ነው፤
9. **"ብርቅዬ የዱር ሕይወት ዝርያ"** ማለት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙና አገሪቱ በብቸኝነት የምትታወቅባቸው የዱር ሕይወት ዝርያዎች ማለት ነው፤
10. **"ሕልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች"** ማለት በተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው ለአደጋ የተጋለጡና ከምድረ-ገጽ ለመጥፋት የተቃረቡ የዱር ሕይወት ዝርያዎች ማለት ነው፤
11. **"አይ ኤ ቲ ኤ "** ማለት ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት ማህበር ነው፤

12. **"መያዣ/ኬጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ማቆያና ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ የሚያገለግል እንደ እንስሳቱ ዓይነት ባህሪና መጠን በሳይተስና አይ ኤ ቲ ኤ ተቀባይነትን ያገኘ የዱር እንስሳት ማቆያና ከቦታ ቦታ ማጓጓዣ ሳጥን ነው፤
13. **"ፍጆታዊ አጠቃቀም"** ማለት የዱር እንስሳትን ከመኖሪያ ቦታው በመውሰድ ወይም በስፖርታዊ አደን፣ በራንች ወይም ዕርባታ በማሳደግ ለውጤታቸው (ሥጋ፣ ቆዳ፣ ላባ፣ቀንድ፣ጥርስ) ሲባል በመግደል የመጠቀም ስልት ነው፤
14. **"ሄርታየልስ"** ማለት በደረት ተሳቢ እና በከፊል በውሃና በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሳትን የሚያካትት ሲሆን ሬፕታየልስንና አምፊብያንስን የሚያጠቃልል የእንስሳት ምድብ ነው፤
15. **"ሳይተስ"** ማለት ሕልውናቸው ለዕልቂት አደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳትና እፅዋት ዓለም አቀፍ ንግድ ስምምነት ነው፤
16. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
17. **"ባለስልጣን"** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፤
18. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፤
19. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
20. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. የዱር እንስሳት ሀብታችንን በፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልቶች ጥቅም ላይ በማዋል ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ፤
2. የዱር እንስሳት በህይወት ንግድ ሥራን ጥራት ባለው መልኩ እንዲስፋፋ ማበረታታት፤
3. ለዱር እንስሳት በህይወት ንግድ ሥራ ወጥነት ያለውን አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በሚከናወኑ የዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የዱር እንስሳት ጠመዳና የሕይወት ንግድ
## ፈቃድ አሰጣጥና መስፈርቶች

5. <u>ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ</u>

1. የዱር እንስሳትን ማጥመድና በሕይወት የመነገድ ፈቃድ የሚሰጠው በባለሥልጣኑ ነው፤ የማጥመድና የመነገድ ፈቃዱ ለሀገር ውስጥ አጠቃቀም ብቻ ከሆነ በክልሎች የሚሰጥ ይሆናል፡፡
2. በክልሎች በህጋዊ መንገድ ተጠምደው በአዲስ አበባ በጊዜያዊነት ለሚቆዩ የዱር እንስሳት የማቆያ ጣቢያው አስፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላቱን ባለሥልጣኑ ማረጋገጫ ይሰጣል፤ በክልሎች ተጠምደው በዚያው ለሚቆዩ ክልሉ የማቆያ ጣቢያው አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
3. የማጥመድና የመነገድ ፈቃዱ ቁጥራቸው የተመናመኑትን፣ በሳይተስ ዕዝል አንድ ላይ የተመዘገቡትን እንዲሁም በአገራችን ብቻ የሚገኙትን ዝርያዎችን አይጨምርም፤ ሆኖም በሀገራችን ብቻ ከሚገኙ የዱር ዝርያዎች ውጭ ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ የማጥመድና የመነገድ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. ባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ዝርያዎች የማጥመድና የመነገድ ፈቃድ የሚሰጠው ቁጥርና ስርጭታቸውን በሚመለከት ወቅቱን የጠበቀ በቂ ሳይንሳዊ መረጃ ሲኖር ነው፡፡
5. የዱር እንስሳት ጠመዳ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ለጠያቂው የሚፈቀድለት የሚጠመዱትን የዱር እንስሳት የነፍስ ወከፍ ዋጋ ክፍያ ገቢ ለማድረጉ የባንክ
6. የዱር እንስሳት በህይወት ከሀገር የማውጫ ፈቃድ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊው ማስረጃ ሲቀርብ በባለሥልጣኑ ይሰጣል፡፡

7. የዱር እንስሳትን በሕይወት የማስመጣትና የመላክ ፈቃድ ለጠያቂው የሚሰጠው በደንቡ ከአንቀፅ 27 እስከ 30 የተጠቀሱትን ግዴታዎች ካሟላ ብቻ ይሆናል፡፡
8. የዱር እንስሳትን በሕይወት የማስመጣትና የመላክ ፈቃድ ዓመታዊ ክፍያ በደንቡ ሰንጠረዥ 2 ተራ ቁጥር 13 ላይ የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 6. <u>የዱር እንስሳት በሕይወት ንግድ መስፈርቶች</u>

ማንኛውም የዱር እንስሳት በህይወት ንግድ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. ግልፅ የአያያዝና የአጠቃቀም ሥርዓትን ያካተተ የተሟላ የፕሮጀክት ሠነድ እና የሥራውን ጭብጥ የሚመለከት ዝርዝር ፕሮግራም፤
2. ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
3. ለየዱር እንስሳቱ ዝርያዎች ተስማሚ የሆነ የማጥመጃ መሣሪያ መሟላት፤
4. የጠመዳ ባለሙያ የሆነ ወይም የጠመዳ ባለሙያና የእንስሳት ሐኪም በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት መቅጠር፤
5. ንፁህ ውሃ መብራትና የራሱ ግቢ ያለው 3 ክፍል የግል ቤት ወይም የአንድ ዓመት የኪራይ ውል ማስረጃ፤
6. በህይወት የሚነገዱት የዱር እንስሳት ደረጃውን በጠበቀና የዱር እንስሳቱን የደህንነት አያያዝ ባረጋገጠ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ የሚያስችል ተስማሚ ተሽከርካሪ ያለው ወይም መከራየት የሚችልና ለየዱር እንስሳቱ ዝርያ ተስማሚ የሆነ ኬጅ፤
7. ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የመንግሥት አካል በሚያሻሽለው የዋጋ ተመን መሠረት መክፈል የሚችል ወይም ለመክፈል ውል የገባ፤
8. በሳይተስ እዝል የተመዘገቡ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትም እንስሳቱ ከሚመጡበት ሀገር የሳይተስ ማውጫ ፈቃድ ማቅረብ፤
9. በሳይተስ እዝል የተመዘገቡ የዱር እንስሳትና ውጤቶችን ወደ ወጪ ሀገር ለመላክ እንስሳቱ ከሚገቡበት አገር የሳይተስ ማስገቢያ ፈቃድ ማቅረብ፤
10. የዱር እንስሳቱን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ለማስወጣት አስፈላጊውን ቀረጥ መክፈል የሚችል፤

7. <u>የዱር እንስሳት ጠመዳ ባለሙያ መስፈርቶች</u>

1. በዱር እንስሳት ጠመዳ እና በሕጋዊ መንገድ የዱር እንስሳትን ከቦታ ቦታ በማዘዋወር ሥራ ቢያንስ የ5 ዓመት ልምድና በዱር እንስሳት አያያዝ ተጨማሪ ሥልጠና
2. የጠመዳ ባለሙያነቱ በባለሥልጣኑ ወይም በክልሉ በሚሰጠው የፅሁፍና ተግባር ፈተና የተረጋገጠ፤
3. ዓመታዊ የፈቃድ ክፍያ በህግ በሚወሰነው መሠረት መክፈል የሚችልና ውል የገባ፣

8. <u>ስለጥያቄ አቀራረብ</u>

1. በዱር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማመልከቻና አስፈላጊ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ ገምግሞ በአንድ ወር ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. የቀረበው ጥያቄ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ በ15 ቀን ውስጥ መረጃውን አሟልቶ እንዲያቀርብ ይመለስለታል፡፡
4. ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የዱር እንስሳትን ማጥመድና በሕይወት መነገድ ተግባራት

9. <u>በጠመዳ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ተግባራት</u>

1. የዱር እንስሳት ጠመዳ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን የሚጠቀመው ለተፈቀደለት የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ብዛት፣ ጾታና የዕድሜ ደረጃ ብቻ ነው፤
2. ባለፈቃዱ ወደ ጠመዳ ሲሰማራ ሙያዊ እገዛ የሚያደርግና ጠመዳው በአግባቡ መከናወኑን የሚያረጋግጥ ቢያንስ አንድ ባለሙያ ከባለሥልጣኑ ወይም ጠመዳው ከሚካሄድበት ክልል ይዞ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

3. ጠመዳው ከመከናወኑ በፊት የዱር እንስሳት ጠመዳ በሚካሄድበት ሥፍራ ያለው የዱር እንስሳቱ ሥነ-ምህዳራዊና ሌሎች ሥነ-ህይወታዊ ክስቶች መጠናት አለባቸው፡፡
4. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለጠመዳ በሚሰማራበት ወቅት የማጥመድ እውቀቱ ከሌለው የጠመዳ ባለሙያ፣ የእንስሳት ጤና ባለሙያ፣ የመጓጓዣ ትራንስፖርት፣ የመያዣ ኬጅ፣ በቂ የሰው ኃይል ፣ የማጥመጃ መሣሪያዎች፣ የመድሃኒት ርዳታ ማግኛ ዘዴዎች በቅድሚያ ማሟላት ይኖርበታል፡፡
5. ጠመዳው የሚካሄደው በአካል በመያዝ ወይም በማደንዘዣ ኬሚካል ከሆነ የሚያዘው የዱር እንሳሳው ዓይነት፣ የኬሚካሉ ዓይነትና ብቃትን በቅድሚያ በሚመለከተው አካል እንዲረጋገጥ ማድረግና ለፈቃጁ ክፍል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
6. ጠመዳ የሚከናወነው በቀን ለሚንቀሳቀሱት ከጧቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ሲሆን፤ ለሌሊት ተንቀሳቃሾች ደግሞ ጠመዳው ባውዛን በማብራት ወይም ሌሎች የማሳያ መሣራያዎችን በመጠቀም በሌሊት ይሆናል፡፡
7. በጠመዳ ወቅት የዱር እንስሳውን አባሮ ለመያዝ ከአራት ደቂቃ በላይ ማስሮጥ አይቻልም፤ እንስሳው በድካምና በድንጋጤ ምክንያት እንዳይጎዳ የውሃና የመድሃኒት እንዲሁም ልዩ ልዩ ርዳታ መደረግ አለበት፡፡
8. የዱር እንስሳት ለረጅም ጊዜ ከእንቅስቃሴ በሚታቀቡበት ጊዜ (Hibernation & aestivation Period)፣ በሚራቡበት፣ በእርግዝናና በሚያጠቡበት ወቅት ማጥመድ አይፈቀድም፡፡
9. ጠመዳውን ለማካሄድ የዱር እንስሳው ላይ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ በቀስት፣ በጉድጓድ ወይም ቁስልና ጣዕር ሊፈጥሩ በሚችሉ መሣሪያዎች መጠቀም አይፈቀድም፡፡

10.<u>ከጠመዳ በኋላ መደረግ ስላለባቸው ተግባራት</u>

1. የተያዙት እንስሳት የሚቆዩበት ቦታ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ሆኖ በማቆያና በማገገሚያ ጣቢያቸው እንደ እንስሳቱ ዓይነትና ብዛት የምግብና የውሃ፣ ምቹ የመኖሪያ ቦታ፣ የሕክምናና ጤና አገልግሎቶች/ የጤና ባለሙያ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡
2. መርዛማ የሆኑ የዱር እንስሳት በማቆያ ጣቢያ መቀመጥ ያለባቸው ጥብቅ በሆነ ኬጅ ወይም ከመስታወት በተሠራ ማቆያ መሆን አለበት፡፡

3. የተጠመዱ የዱር እንስሳት በማቆያ ጣቢያ ከአንድ ወር በላይ መቆየት የለባቸውም፡፡
4. በማቆያ ቦታው የሚገኙት የዱር እንስሳት ወደ ውጭ ከመላካቸው በፊት አስፈላጊው ፈቃድና የጤንነት ሠርተፊኬትና የተሟሉ የዓለም ዓቀፍ የመጓጓዣ መስፈርቶች መሟላታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
5. የማቆያ ጣቢያው የዱር እንስሳቱን ሁኔታና አጠባበቅ ለመመልከትም ሆነ ለመፈተሽ ለሕጋዊ ተቆጣጣሪ በማንኛውም ወቅት ክፍት መሆን አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ ወደ ውጭ የሚላኩ የዱር እንስሳት መያዣ ወይም ኮንቴነር ላይ መነሻና መድረሻውን አገር እንዲሁም የዱር እንስሳውን ዓይነትና ብዛት በጽሁፍ ያረጋግጣል፡፡
7. የሚላኩት የዱር እንስሳት በሕጋዊ የመውጫ በሮችና ዓይነታቸው ትክክል ለመሆኑ በሕጋዊ ተቆጣጣሪ መረጋገጥና መፈቀድ ይኖርበታል፡፡
8. ላኪው እንስሳቱን በሚልክበት ወቅት የባለሥልጣኑ ባለሙያ በመላኪያው ሥፍራ ተገኝቶ እንዲቆጣጠር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለዱር እንስሳት ጠመዳና አያያዝ

### 11. ስለዱር እንስሳት መያዣ /ኬጅ/ አሠራር

1. ለሁሉም ጡት አጥቢ የዱር እንስሳት የሚያገለግል መያዣ /ኬጅ/ እንደ ዱር እንስሳው ግዙፍነት፣ ጉልበትና የአመጋገብ ዓይነት ከእንጨትና ሽቦ ወይም ከብረት መሠራት አለበት፡፡
2. እንደ ዱር እንስሳቱ ዕድሜና እርስ በእርስ የመቀራረብ ሁኔታና በአንድ ኬጅ ውስጥ ምን ያህል ማቆየት እንደሚቻል በባለሥልጣኑ ወይም በክልሉ ባለሙያ መወሰን አለበት፡፡
3. ለተለያዩ የዱር እንስሳት ማጓጓዣ የኬጅ አሠራር የሳይተስ እና የአይ.ኤ.ቲ.ኤ መመሪያን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## 12. የሄርፕታይሎች መያዣ ኬጅ

1. የእባብ መያዣ ለአራት እባቦች ብቻ የተሠራ ሆኖ፣
   ሀ. ስፋቱ የረጅም እባብን ርዝመት ከ1 ሜትር እስከ 1 ሜትር ተኩል፤
   ለ. የማረፊያ ድንጋይ፣ መጠለያ፣ ውሃ ማስቀመጫና መንቀሳቀሻ ያለው መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ ለመጨመር ሲያስፈልግ መያዣው በእያንዳንዱ እባብ 25 በመቶና ከዚያ በላይ መስፋት አለበት፡፡
3. የእንሽላሊትና ገበሎ መያዣ ለሁለት እንሽላሊትና ገበሎ ለየብቻ የሚሠራ ሆኖ፣
   ሀ. ከ2 እስከ 12 ኢንች ርዝመት ላላቸው ስፋት 20 X10 ኢንች እና 15 ኢንች ርዝመት፤
   ለ. ከ12 እስከ 13 ኢንች ርዝመት ላላቸው ስፋት 30X15 ኢንች እና 15 ኢንች ርዝመት
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው ቁጥር በተጨማሪ ሁለት እንሽላሊትና ገበሎ በመያዣው መጨመር ቢያስፈልግ እንደ እንስሳቱ የሰውነት መጠን መያዣ /የኬጅ/ መጠን ከ2 ኢንች እስከ 12 ኢንች ድረስ በቁመት ስፋት መጨመር አለበት፡፡

## 13. ስለጡት አጥቢ የዱር እንስሳት አያያዝ

1. ጡት አጥቢ የዱር እንስሳትን የኬሚካል ማደንዘዣ መድሃኒቶችን በመጠቀም ወይም በማሯሯጥ ወይም የዱር እንስሳው በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ጎጂ ያልሆነ ወጥመድ /የናይለን መረብ ወይም ምግብ በማስቀመጥ/ መያዝ ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው ውጪ ሌሎች የመያዣ ዘዴዎችን ለመጠቀም በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጭው አካል ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
3. ኃይለኛና ግዙፍ ለሆኑ የዱር እንስሳት ለዚሁ በተዘጋጀው ቀስት ወይም በተመሳሳይ መሣሪያ አማካኝነት የዱር እንስሳውን የሚመጥን ኬሚካል ተጠቅሞ በማደንዘዝ

በተዘጋጀለት ሣጥን ውስጥ አስገብቶ አስፈላጊውን መድሀኒት በመስጠት እንስሳው እንዲረጋጋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 14. ስለአዕዋፍ አያያዝ

አዕዋፋትን የማይጎዳ ወጥመድ ወይም መረብ በመጠቀም መያዝ የሚቻል ሆኖ፤

1. የጅግራና ቆቅ ዝርያዎችን መረብ በተዘረጋበት አቅጣጫ እንዲሸሹ በማባረር፣
2. አነስተኛ ጥራጥሬ የሚመገቡ አዕዋፋትን በሚከደን ወጥመድ ሥር ጥራጥሬ በማድረግ፣
3. ሥጋ በል አዕዋፋትን ሊዘጋ በሚችል ወጥመድ ውስጥ ሥጋ በመጨመር፣
4. ሰጎንን ከ3 እስከ 4 ደቂቃ በመኪና በማሯሯጥ

መያዝ ይቻላል፡፡

## 15. ስለሄርፕታይሎች አያያዝ

1. ለጠመዳ የተፈቀዱ እንቁራሪቶችን መያዝ የሚቻለው በእጅና በመረብ ብቻ ይሆናል፡፡
2. እባብን መያዝ የሚቻለው የእባብ መያዣ ዘንግ፣ መረብ ወይም ከረጢት በመጠቀም ይሆናል፡፡
3. ከዚህ ውጭ ሌሎች ለአደን የተፈቀዱ ሄርፕታይሎችን መያዝ የሚቻለው እንስሳቱን ሊጎዱ ወይም ሊያቆስሉ በማይችሉ መሣሪያዎች ብቻ ይሆናል፡፡

## 16. ስለ ክትትልና ቁጥጥር

1. ለጠመዳ በሚፈቀዱ ቦታዎች የባለሥልጣኑና የክልል ባለሙያዎች ድንገተኛ ቁጥጥር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
2. ሕጋዊ ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳትን ሲያጠምድ የተገኘ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀፅ 16 እና በደንቡ አንቀጽ 17 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ

ማንኛውም የዱር እንስሳትን ለመነገድ ወይም ለማጥመድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡፡

1. ከብሔራዊ ፓርኮችና ከመጠለያዎች፣ ከጥብቅ ክልሎችና ከቁጥጥር አደን ቀበሌዎች እንዲሁም ከሕብረተሰብ የጥበቃ ቦታዎች ውጭ በተፈቀደለት ቦታ ውስጥ ብቻ የዱር እንስሳትን የማጥመድ፤
2. ለማጥመድ በሚፈቀድለት ቦታ የሚገኙትን የዱር እንስሳት የመጠበቅና በቀጣይነት ለዘለቄታዊ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የመንከባከብ፣
3. የእንስሳቱን የመኖሪያ አካባቢ የሚበክል/ የሚያውክ ማንኛውም ዓይነት መሣሪያ ወይም ኬሚካል ወይም በህግ ያልተፈቀዱ ነገሮችን ያለመጠቀም፣
4. ለሕይወት ንግድ ያልተፈቀዱ የዱር እንስሳትን በስህተት በሚይዝበት ጊዜ ወዲያውኑ ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው የመልቀቅ፤
5. ማንኛውም አጥማጅ የጠመዳ ስራ ሲያጠናቅቅ የተሰጠውን የጠመዳ ፈቃድ ለሰጠው አካል የመመለስ፣
6. አጥማጁ የዱር እንስሳውን በሚያጠምድበት ወይም በሚያጓጉዝበት ወቅት በእንስሳቱ ላይ የደረሰውን ጉዳት ወይም ሞት ከነምክንያቱ ለፈቃድ ሰጪው አካል የማሳወቅ፤
7. ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የአገሪቱን ህጎች የማክበር፡፡

## 18. <u>ግዴታን ባለማክበር ስለሚወሰድ እርምጃ</u>

ማንኛውም የዱር እንስሳ በሕይወት ለመያዝ የተፈቀደለት ሰው፡-

1. ከተፈቀደለት ዱር እንስሳ ዝርያ/ዓይነት፣ ቁጥር እና የማጥመጃ ቦታ ውጭ ሲያጠምድ ቢገኝ ያጠመዳቸውን የዱር እንስሳት ዋጋ ከፍሎ የሥራ ፈቃዱ ለ2 ዓመት እንዲታገድ ይደረጋል፣ የያዛቸውንም የዱር እንስሳት በተያዙበት ቦታ መልቀቅ አለበት፡፡
2. በተከለከሉ የማጥመጃ መሳሪያዎችና ዘዴዎች ሲያጠምድ ቢገኝ የተጠቀመው መሣሪያና ዘዴ በዱር እንስሳቱና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ እንደሚያደርሰው ጉዳት መጠን ፈቃዱ ከ1 (አንድ) እስከ 3(ሦስት) ዓመት እንዲሠረዝ ይደረጋል፡፡
3. የሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ላልተፈቀደለት ሕገወጥ ተግባር ሲያውል፣ የዱር እንስሳትን በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር ሲያስወጣ፣ በሕይወት በሚያዙ የዱር እንስሳት

ላይ ጭካኔ የተላበሰ ድርጊት ሲፈጸም፣ በተደጋጋሚ ልዩ ልዩ ጥፋቶችን ሲፈጽም፣ የተሰጠው ፈቃድ ተሠርዞ ላጠፋው ጥፋት አግባብነት ባለው ህግ ይጠየቃል፡፡

4. ለጠመዳ የተሰጠውን ፈቃድ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሳያድስ ቢቀር ፈቃዱ ለስድስት ወር ይታገዳል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 20. <u>ስለፈቃድ እድሳት</u>

በደንቡ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የድር እንስሳት ጠመዳና የህይወት ንግድ ፈቃድ የሚያገለግለው ለስድስት ወራት ብቻ ሲሆን፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ መታደስ ይኖርበታል፡፡

### 21. <u>ቅጣት</u>

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

### 22. <u>ቅሬታ ስለማስተናገድ</u>

1. በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

### 23. <u>የስራ ማንዋል ስለማውጣት</u>

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ዝርዝር የሆነ የስራ ማንዋል ያወጣል፡፡

## 24. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡